# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 209 ግንቦት 9 2004 ገጽ 1

**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የግንቦት 7 ቀን 1997 ትሩፋት በግንቦት 20 ቀን 1983 እርግማን ላይ ፍጹም የሆነ ድል እንዲቀዳጅ ተግቶ ይሰራል። ብርሃን ጨለማን ድል ይነሳል። የግንቦት 7 ትሩፋት የግንቦት 20 እርግማንን ጠራርጎ ያጠፋል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የህዝብ ድምጽ በመስረቅ አገራችንን ወደ አለመረጋጋት የመለሰበት 7ኛ አመት አስመልክቶ ግንቦት 7 መግለጫ አወጣ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በ1997 ዓ.ም. በተገኘው ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል የተበረታታው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያስደንቅ ትዕግሥትና ሥነሥርዓት ለምርጫ ቀርበው ከነበሩት ውስጥ "ይወክሉኛል፤ ይመሩኛል" ያላቸውን እጩዎች በነቂስ ወጥቶ የመረጠበት የግንቦት 7 1997 አም 7ኛ አመትንና በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ በምርጫው ቀን ማግሥት የሰረቀውን የህዝብ ድል ለማስመለስ ድርጅታችን የተቋቋመበትን 4ኛ አመት ለመዘከር በዛሬው ዕለት ባወጣው መግለጫ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ፤ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ እና በየቦታው ያስቀመጣቸው ምስለኔዎች አለመሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ ሲገልጽ መለስ ዜናዊ አጥልቆት የነበረውን የዲሞክራሲ ጭንብሉን አውልቆ በመጣል የንጹሃን ዜጎችን ደም በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ጎዳና ላይ በማፍሰስ እውነተኛውን ዘረኛና ፋሽስታዊ ገጽታውን ለኢትዮጵያና ለመላው አለም አሳይቶአል ብሎአል።

የህዝብን ድምጽ በመቀልበስ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ በመላው አገሪቱ ባሰማራው ገዳይ የአጋዚ ጦር የተጨፈጨፋት ወገኖቻችን ቁጥር የትየሌለ መሆኑን የጠቀሰው የግንቦት 7 መግለጫ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ወያኔ እራሱ በወቅቱ ባቋቋመው የአጣሪ ኮሚሽ ይፋዊ መረጃ መሠረት ወደ 200 የሚጠጉ ኢትዮጵያዊያን በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ መገደላቸውን አስታውሶ በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች ሳይመዘገቡ ከቀሩት በርካታ ግዲያዎች በተጨማሪ ከ40 ሺህ በላይ ወጣቶች ታስረው በረሃ ውስጥ ለስቃይ እንደተዳረጉና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የተለያዩ አይነት የአካል ጉዳት ሰላባ እንደሆኑ ገልጾአል።

ነጻና ገለልተኛ የሆኑ ተቋሞች በሌሉበት የተሰረቀውን የህዝብ ድምጽ ለማስመለስ የተደረጉ ሰላማዊ ጠረቶች በሙሉ ወያኔ በእብሪተኝነት በወሰዳቸው የሃይል እርማጃዎች ተጨፍልቆ የሚሊዮኖች ኢትዮጵያዊያን ቅስም ተሰብሯል ያለው የግንቦት 7 መግለጫ፤ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ በወሰደው በዚህ እርምጃው የአንድን ትውልድ ተስፋ በማምከን በአገሪቷ ላይ አቻ የሌለው አውዳሚ ተግባር ፈጽሞአል ሲል ከሶአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግንቦት ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 3 ያንቡ

## መለስ ዜናዊ በአገራችን ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ወንጀል እንዲያቆም የሚጠይቅ የተቃውሞ ሰልፍ በአውሮጵያ ህብረት ጽ/ቤት ፊት ለፊት ተካሄደ

የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገራችንና በህዝባችን ላይ የሚፈጽማቸውን የመብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲያቆም ለመጠየቅ በትናንትናው ዕለት ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ የአውሮጳ ኮሚሽን የጸጥታና የውጪ ግንኙንት ሃላፊ ቢሮ ፊት ለፊት መካሄዱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከብራስል በላከው ዜና አስታወቀ።

በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለመገኘት በርካታ የአፋሪ ኮሚኒቲ አባላት ከታላቂቷ ብሪታኒያ፤ ከስዊድንና ከጀርመን ድረስ መምጣታቸውን የዘገበው ዘጋቢያችን በበልጂዬም አጎራባች አገር ሊክስምበርግና ሆላንድ የሚኖሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያን ጭምር በመሳተፍ ለተቃውሞ ሰልፉ ድምቀት መስጠታቸውን አስታውቆአል።

ሰላማዊ ሰልፉን የጠራው በቤልጂዬም የኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ፤ የአፋር ሰብአዊ መብት ድርጅትና ሉቅማን የኢትዮ ቤልጄያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ማኅበር እንደሆነ በታወቀው በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ሲስተጋቡ ከነበሩት መፈክሮች መካከል፤ መለስ ዜናዊ ፋሽስት ነው፤ መለስ ዜናዊ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ በአፋር፤ በጋምቤላ፤ በኦሮሚያና በሱማሌ ክልሎች የሚደረጉ የመሬት ንጥቂያዎች በአስቸኳይ ይቁም፤ ዜጎችን ከመሬታቸው ማፈናቀል ይቁም፤ ህዝብን ማዕከል ያላደረገ ልማት ጥፋት እንጂ ልማት አየደለም፤ ከደቡብ ክልል በአማራነታቸው ብቻ ተለይተው የተባረሩት ዜጎች አሁኑኑ ወደ ነበሩበት ይመለሱ፤ ዘጎችን በብሄረሰብ ማንነታቸው ማጥቃት ይቁም፤ የሙስሊሙ እምነት ተከታዮችን ለመከፋፈል የሚደረገው ጥረት በአስቸኳይ ይቁም፤ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳው የመብት ጥያቄ የሁላችንም ጥያቄ ነው፤ በሼሪያን ህግ መተዳደር የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጥያቄ አይደለም (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የዘረኛው መለስ ዜናዊን በጂ 8 ስብሰባ ላይ መጋበዝ በመቃወም ኢትዮጵያዊያን ተቃውሞ እያሰሙ ነው

የፊታችን ቅዳሜ በአሜሪካን አገር በካምፕ ደቪድ የሚደረገውን የ8ቱ ባለጸጋ አገሮች ስብሰባ ላይ የተጋበዘውን አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊን በመቃወም በሰሜን አመሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በትናትናው ዕለት ግንቦት 6 በዋይት ሃውስ ፊት ለፊት ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው ታውቆአል።

ዜጎችን በማፈንና በመግደል ስልጣን ላይ ላለፉት 21 አመታት በሃይል የኖረውን መለስ ዜናዊ በእንዲህ አይነት አለም አቀፍ ስብሰባ መጋበዚ ለሚፈጽማቸው ወንጀሎች እውቅና እንደመስጠት ይቆጠራል ያሉት ተቃዋሚዎች ፕሬዛዳንት አባማ በአፍሪካ ውስጥ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ለመስራት ቃል የገቡትን በማጠፍ ከመለስ ዜናዊ አይነቶቹ ነፍሰ ገዳዮች ጋር ስብሰባ መቀመጣቸው እጅግ እንዳስዘናቸው ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ተቃውሞዋቸውን አሰምተዋል።

በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የሲቪክ ማህበራት፤ ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለአንድነትን እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች በተሳተፉበት በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ኢትዮጵያዊያኑ ጭምር በሚከፍሉት የታክስ ገንዘብ ዘረኛውን መለስ ዜናዊ በገንዘብ ድጋፍ ማጠናከራቸው አንሶ ይህንን ነፈሰ ገዳይ በዚህ ስብሰባ እንዲገኝ በመጋበዛቸው የተሰማቸውን ቁጣ አሰምተዋል።

ኢትዮጵያዊያኑ ሰልፈኞች በዋይት ሃውስ ፊት ለፊት ካደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ በተጨማሪ በዋሽንግተን ዲስ በሚገኘው የህንድ ኤምባሲ ፊት ለፊት ተገኝተው መለስ ዜናዊ የአገሩን ዜጎች እያፈናቀለ የሚቸበቸበው መሬት መቀራመት ላይ የተሰማሩ የህንድ ዜጎች ህገወጥ ተግባር እየፈጸሙ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ድምጻቸውን አሰምተዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት (መጅሊስ) ፕሬዝዳንት መለስ ዜናዊ ለደህንነታቸው ባመቻቹላቸው ቤት ውስጥ መኖር እንደጀመሩ ተዘገበ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት (መጅሊስ) ፕሬዝዳንት ሽህ አህመዲን ሽህ አብድላሂ ጨሌ የወያኔው አገዛዝ ለደህንነታቸው ሲል ባመቻቸላቸው ቤት ውስጥ መኖር መጀመራቸውን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ማስታወቃቸውን ኢሳት ዘገበ፡፡

የኢሳት ምንጮች ለቴሌቪዥን ጣቢያው እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ እና አካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ በአወሊያና ሌሎች መስኪዶች የመጅሊስ ይፍረስና የኢህአዴግ መንግሥት በላያችን ላይ በሥልጠና በግድ የሚጭነውን የአሕባሽ አስተምህሮ ያንሳልን ሲሉ የተጠናከረ ጥያቄ ማንሳት ከጀመሩ ካለፉት አራት ወራት ጀምሮ መጅሊሱ የሰጣቸውን ፒያሳ በኒ መስጂድ ገባ ብሎ የሚገኘውን መኖሪያ ቤታቸውን ለቀው ጦር ኃይሎች ቶታል አካባቢ ቀደም ሲል የትምህርት ሚንስትር የነበረቺው ገነት ዘውዴ ትኖርበት ወደ ነበረው አምስት መቶ ካሬ ሜትር ላይ ተንጣሎ ከሚገኘውን ቪላ ቤት መግባታቸውና 24 ሰዓት ሙሉ በደህንነት ሰዎች እየተጠበቁ መሆናቸው ታውቆአል።

ከወያኔ ጋር ሚሥጥራዊ ሥምምነት በማድረግ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ የአሕባሽን አስተምህሮ በግድ በሥልጠና እንዲሰጥ የተባበሩት ሽህ አህመዲን ሽህ አብድላሂ በመጪው ሁለት ወራት ውስጥ ሥልጣናቸውን ይለቃሉ ቢባልም የሙስሊሙ ማህበረሰብ ያካሂደዋል የተባለው ምርጫ በቀበሌና በዑላማዎች ምክር ቤት ስለሚካሄድ ተመልሰው የመመረጥ አሊያም ደጋፊዎቻቸው ቦታውን እንደሚይዙ በወያኔ ቁንጮዎች ቃል እንደተገባላቸው ኢሳት ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው ሰዎች መረጃ ማግኘቱን ዘግቦአል።

ይህ በዚህ እንዳለ በአቡነ ጳውሎስ አማካይነት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ለቀናት እየታመሰ መሆኑን ደጀ-ሰላም ዘገበ።

ድረ-ገጹ የስብሰባ ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው፤ችግሩ የተጀመረው ገና ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ዝርዝር የመወያያ አጀንዳዎቹን ለምልአተ ጉባኤው ሲያቀርብ ነው።

ኮሚቴው ካቀረባቸው 20 አጀንዳዎች ውስጥ ርእሰ-መንበሩ አቡነ ጳውሎስ በተራ ቁጥር 18 ላይ በሰሜን *አሜሪካ በስደት ከሚገኙ አባቶች ጋራ የተጀመረው ዕርቅ ጉዳይ* በአጀንዳነት መያዙን ይቃወማሉ።

የእርቁ ጉዳይ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትም "ፖሊቲከኞች ናቸው" በሚልም በዕርቀ- ሰላሙ ሂደት መቀጠል ላይ እንደማያምኑበት ይናገራሉ።

አቡነ ጳውሎስ በዚህ ሳያቆሙም ከመንበረፓትርያርኩ ተወክለው ከሄዱት ልኡካን መካከል አንዱን አባል በስም በመጥቀስ፡-*"ወደኋላ ቀርተው ከእነርሱ ጋራ ነገር ሲሸርቡብኝ ነበር"* በማለት ወቀሳ እንደሰነዘሩ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የግንቦት 20 ጨለማ እና የግንቦት 7 ብርሃን በአዲስ አበባ!

ግንቦት ወር አንድ የጨለማ እና አንድ የብርሃን መታሰቢያ ቀናት አሉት። የመጀመሪያው የ1983ቱ ግንቦት 20 ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የ1997ቱ ግንቦት 7 ናቸው።

ሁለቱ ቀናት አዲስ አበባ ውስጥ እንዴት እንደነበሩ ማስታወሱ የቀናቱ ታሪካዊ ዋጋ ገላጭ ነው።

ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባይተዋር ሆኖ ስልጣን ከአንድ አምባገነን ወደሌላ አምባገነን የተሸጋገረበት እለት ነው። በዚህ እለት፣ አዲስ አበባ ፍርሃት የነገሠባት፤ ተስፋ የራቃት፤ ጨለማ የዋጣት ከተማ ነበረች። የመንግሥት ሥልጣን ሕዝብ ከሚያውቀው ሰይጣን ማንም ወደ ማያውቀው ሰይጣን ሲተላለፍ የአዲስ አበባ ሕዝብ በከፍተኛ ግራ መጋባትና ፍርሃት ይታዘብ ነበር። የአዲስ አበባ ሕዝብ አዲስ አበባ ውስጥ እየሆነ ስላለው ጉዳይ የሚያውቀው ጉዳይ አልነበረም። የማያውቃቸው ሰዎች ስልጣን ሲከፋፈሉ፤ ትዕዛዝ ሲሰጡ፤ ሲደራደሩ የሚሆነው በፍርሃት ከመጠበቅ ውጭ አንዳችም የሚያደርገው ነገር አልነበረም። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርሃት ዋጣት። ነዋሪዎቿ በጊዜ በየቤታቸው ተከተቱ፤ በሮቻቸውንም አጥብቀው ዘጉ። እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ያም ሌሊት ይነጋ እንደሆን እንኳን እርግጠኛ መሆን ለብዙ ሰዎች ያዳገተ የጭንቅ ለሊት ነበር።

ግንቦት 7 1997 ግን የዚህ ቀጥተኛ ተቃራኒ ነበር። የምርጫ ካርድ የያዘ እያንዳንዱ የአዲስ አበባ ነዋሪ የእርሱ ካርድ የምርጫውን ውጤት የምትወስን ወሳኝ ድምጽ የሆነች ያህል ተሰምቶት ነበር። በእርሱ አንዷት ካርድ የሃገር እድል የሚወሰን አድርጎ የተመለከተው መራጭ፣ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት ረዥሙን ሰልፍና ከራራውን ፀሃይ የተቋቋመው በደስታ ነው። በእለቱ እናቶችና አባቶች ከራሳቸው ይልቅ ለልጆቻቸው የተሻለ ጊዜ የመጣ መሆኑን በማሰብ ልቦቻቸው በሃሴት ተሞልተው ነበር። ግንቦት 7 ቀን ሁሉም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ውሳኔ ሰጭ ነበር። እንዳንዳንዱ ሰው የጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት ነበር። ግንቦት 7 ቀን 1997 በአዲስ አበቤዎች ልብ ውስጥ ተስፋና ፍቅር ሞልቶ ነበር።

ግንቦት 20ን ዘንድሮ ሃያ አንድ ዓመት ሊሞላው ነው። በከረመ መጠን የግንቦት 20 ጨለማነት እየባሰ መጥቶ ዛሬ ኢትዮጵያችንን እድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ከቷታል። በግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሥጋት ውስጥ የነበሩ ቢሆን እንኳን ቢያንስ በራሳቸው አገር ውስጥና በራሳቸው ከተማ ውስጥ ስለመሆናቸው ጥርጣሬ አልነበራቸውም። አሁን ግን ያ ስሜት የለም። የዛሬዋ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዊያን እንዳልሆነች ሁሉ አዲስ አበባም የቀድሞ ነዋሪዎቿ ከተማ አይደለችም። አዲስ አበባ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ መዲና ሆናለች። ዛሬ አዲስ አበባ የመለስ ዜናዊ ባለሚሎችና አገልጋዮች የዘረፉት ሃብት ማከማቻና የሃብታቸው ብዛት ማሳያ ከተማ ሆናለች። አዲስ አበባ የመለስ ዜናዊ ጆሮ ጠቢዎች፣ ደላሎች፣ ተላላኪዎችና ካድሬዎች የሚንፈላሰሱባት፤ ሌላው ነዋሪ ግን አፉን ከንግግርም ከምግብም አቅቦ የሚውልባት እስር ቤት ሆናለች።

ድሮ ከየትኛው የኢትዮጵያዊ ግዛት የመጣ ኢትዮጵያዊ አንገቱን ቀና አድርጎ እንዳልተራመደባት ዛሬ አዲስ አበባ "ምርጥ ዘር ነን" ባዮች ብቻ የሚጎላመሙባት፤ ሌላው አንገቱን ደፍቶ የሚሽለኮለኩባት ከተማ ሆናለች።

አዲስ አበባ በዘር የሚበላባት፤ በዘር የሚሾምባት፤ በዘር የሚሸለምባት ከተማ ሆናለች። አዲስ አበባ ሰው በዘሩ ምክንያት የሚታሰርባት፤ ታስሮም በዘሩ ምክንያት ሰቆቃ የሚፈጸምባት ሲዖል ሆናለች። በግንቦት 20 ጦስ አዲስ አበባ "አዲስ አበባነትዋን" አጥታ በባለጊዜዎች ሰፈር መታየት ወንጀል የሆነባት የድሮዋ ፕሪቶሪያ ሆናለች።

ታድያ ይኸ ሁሉ እየሆነም ቢሆን አዲስ አበባ የግንቦት 7 ቀን 1997ን ትሩፋት ሙሉ በሙሉ አላጣችም። ጨለማ የቱን ያህል የገዘፈ ቢመስል ብርሃንን ማሸነፍ አይቻለውም። ትንሽ ብልጭታ ድቅድቁን ጨለማን ድል እንደሚነሳ ሁሉ በግንቦት 7 ትሩፋት የግንቦት 20 እርግማን ተጠራርጎ እንደሚያጠፋ አዲስ አበቤዎች እርግጠኞች ናቸው።

ይህ ጽኑ እምነት የአዲስ አበቤዎች ብቻ አይደለም። ይህ እምነት የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት ነው። ግንቦት 20 ይዞብን የመጣው እርግማን በግንቦት 7 ትሩፋት ተጠራርጎ እንደሚጠፋ እኛም እርግጠኞች ነን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የግንቦት 7 ቀን 1997 ትሩፋት በግንቦት 20 ቀን 1983 እርግማን ላይ ፍጹም የሆነ ድል እንዲቀዳጅ ተግቶ ይሰራል። ብርሃን ጨለማን ድል ይነሳል። የግንቦት 7 ትሩፋት የግንቦት 20 እርግማንን ጠራርጎ ያጠፋል።

የግንቦት 7 ተምሳሌነት አብሮን ይኖራል፤ ብርታትም ይሰጠናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!**

---

## ግንቦት 7ን ለ7ኛ ጊዜ ስንዘክር

ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ ግንቦት 7 2004 ዓ.ም

እነሆ ግንቦት 7 ቀን 1997ን ለ7ኛ ጊዜ እንዘክራለን።

በ1997 ዓ. ም. በተገኘው ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል የተበረታታው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያስደንቅ ትዕግሥትና ሥነሥርዓት ለምርጫ ቀርበው ከነበሩት ውስጥ "ይወክሉኛል፤ ይመሩኛል" ያላቸውን እጩዎች መረጠ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ እና በየቦታው ያስቀመጣቸው ምስለኔዎች አለመሆናቸው በማያሻማ ሁኔታ ሲታወቅ መለስ ዜናዊ አጥልቆት የነበረውን የዲሞክራሲ ጭንብሉን አውልቆ በመጣል እውነተኛውን ዘረኛና ፋሽስታዊ መልኩን አሳየ። ይህ ዘረኛና ግፈኛ የሥርዓቱ ቁንጮ በማግሥቱ ግንቦት 8 ቀን ራሱ በቴሌቪዥን ቀርቦ ባነበበው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አገሪቷን አመሰ። ዘረኝነትና ጥላቻን የታጠቀ የመለስ ዜናዊ ገዳይ ሠራዊት የኢትዮጵያን ከተሞችና ገጠሮችን አጥለቀለቁ። የአዲስ አበባ እና የሌሎች ትላልቅ ከተሞች መንገዶች በደም ታጠቡ። ፋሽስታዊ ዘረኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ነገሠ።

በግንቦት 7 1997 ምርጫ ሰበብ ሺህዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የተለያዩ የአካል ጉዳቶች ደርሰውባቸዋል። ከዚህ ቁጥሩ እጅግ በላይ የሆነ ሕዝብ ምናልባትም በሚሊዮኖች በሚቆጠር ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሥነልቦና ጉዳት ደርሷል። የምርጫ 97ን ሕዝባዊ ድል ለማስጠበቅ ባለመቻላችን ምክንያት እና ይህንኑ የአቅም ማነስ ተከትለው በመጡ ተጨማሪ ችግሮች ሳቢያ የሚሊዮኖች ኢትዮጵያዊያን ቅስም ተሰብሯል።

ግንቦት 7 ቀን 1997 የምናስታውሰው እንዲህ በተደባለቀ ስሜት ነው። በአንድ በኩል ነፃነት ካገኘ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዎቹን መምረጥ የሚችል መሆኑ ያረጋገጠበት እለት በመሆኑ ግንቦት 7 ቀን 1997ን የምናስታውሰው በሃሴት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዲሞክራሲ ማለት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ ማለት አለመሆኑ በተግባር የተረዳንበት እለት ነው። ዲሞክራሲያዊ ተቋማትና ባህል በሌሉበት ሁኔታ በምርጫ የተገኘው ሕዝባዊ ድል ለሃያ አራት ሰዓታት እንኳን አለመዝለቁ የምናስታውሰው በቁጭት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት 7 ቀን 1997 ከምርጫ ሳጥን ያገኘውን ድል ብቻ ሳይሆን በሰላማዊ ምርጫ መንግሥትን መሾምና መሻር ይቻላል የሚለው ተስፋው ጭምር የተነጠቀው ድሉን የሚያስጠብቅለት ድርጅት፣ ተቋም፣ ህግ፣ ሥርዓትና ባህል ስላልነበረ ነው።

ይህ ቁጭት ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ላይ "ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን" ወለደ። በዚህም ምክንያት ግንቦት 7 ድርብ በዓል ሆነ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ (ግንቦት 7) የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት 7 1997 አግኝቶት በማግሥቱ ያጣውን ድል ለማስመለስ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

የግንቦት 7 ራዕይ "እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኝበት፤ የዜጎች ህይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።"

የግንቦት 7 ተልዕኮ ደግሞ "የመንግሥትና የፖለቲካ ሥልጣን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያዝበት፤ የሃገሪቱ ዜጎች ምርጫ በተግባር የሚገለፅበት፤ ማኅበራዊና የፖለቲካ ችግሮች በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚፈቱበት እና ዲሞክራሲያዊ ባህል የሚበለፅግበት ብሄራዊ የፖለቲካዊ ሥርዓት መገንባት ነው።"

የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዎቹን የመሾምና የመሻር መብቱ ተስፋው ከተነጠቀ ሰባት፤ ይህንን ተስፋ ለማስመለስ የተነሳው ንቅናቄ ከተቋቋመ ደግሞ አራት ዓመታት ተቆጥረዋል።

ከግንቦት 7 ቀን ከ1997 ዓም ወዲህ በነበሩት ሰባት ዓመታት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወደ ፍጹማዊ አምባነንነት የተሸጋገረበት ጊዜ ነው። መለስ ዜናዊ የመንግሥትን ሥልጣን በቤተሰብ የያዘበት፤ የሃብት ዘረፋ ተሰምቶ እማይታወቅበት ደረጃ የደረሰበት ጊዜ ነው። በእነዚህ ሰባት ዓመታት ውስጥ የመለስ ዜናዊ ዘመዶችና አጫፋሪዎቹ በሃብት ላይ ሃብት፤ በምቾት ላይ ምቾች ሲደራርቡ ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን የእለት ጉርሱን እንኳን ማግኘት ወደማይችልበት የድህነት ደረጃ ወርዷል። ኢትዮጵያዊያን የልባቸውን መናገር ቀርቶ ማሰብ እንኳን እንዳይችሉ ስታሊንም ሆነ ሂትለር ያልተጠቀሙበትን የፀረ-ሽብር ህግ የሚባል አውጥቶ የኢትዮጵያዊያንን አንደበትና ህሊና ለመዘጋት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝበት ወቅት ነው። ወያኔ በድህነት ያዳከመውን ኢትዮጵያዊ "ወይን ለኑሮ" በሚባል አዋራጅ ስልት ለመኖር ሲል የሥርዓቱ ተባባሪ እንዲሆንለት ለማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ ጥረት እያደረገ ያለበት ጊዜ ነው።

ይህንን አዋራጅ ሁኔታ ለመቀየር ነው በግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተደራጀው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# አሁን ያላዘነ ማን ነው ?

ዛሬ ኢትዮጵያዊያን አገር እያለን አገር አልባ እንሆን ዘንድ መለስ ዜናዊና ጥቂት ጨካኝ ጉጅሌዎቹ ፈርደውብናል። መንድራችንን በርብረው ያለንን ሁሉ የራሳቸው አድርገዋል። ብዙ የአገራችን ገበሬዎች መሬት አልባ ሲሆኑ እነርሱ በአርሶ አደሩ መሬት ላይ እየፈነጩበት ይገኛሉ። ከጥጋባቸው ወደር ማጣት የተነሳም የምታመልኩትን እኛ እንመረጥላችሁ እያሉን ነው። የለም እኛ የምናመልከውን እናውቃለን ባሉ ሙስሊሞች ላይ ግድያ ፈጽመዋል።የቀሩትንም ዘብጥያ አውርደዋቸዋል።

በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ያልተበረበረ ምድር ያላለቀሰ ዜጋ የለም። በጋምቤላ ጨኸት በርክቷል። በኦሮሞዎች ላይ የተመዘዘው ሰይፍ ወደሰገባው አልተመለሰም። በአማሮች ላይ የተወጠረው የጥላቻ ቀስት አልረገበም። ኦጋዴን እሪ እያለ ነው።በአፋር ሮሮው ጽዋውን ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። ወልቃይት ሰው አልባ ሁናለች።

በመስኪዶቻችን ውስጥ በተከበረው ወንበር ላይ ነውረኛ ግለሰቦች ተቀምጠዋል። ዮዲት ጉዲት እንዳደረገችሁ ሁሉ አብያተ ክርስትያናትና ገዳማቶቻችንም ተዋርደዋል። ሆን ተብለው በሙስሊሙና በክርስትያኑ መካከል ግጭት ለመፍጠር ታስቦ በእሳት እንዲጋዩ የተደረጉ ገዳማትና አብያተ ክርስትያናትም አሉ። የንጹሃን ደምም በከንቱ እንዲፈስ ተደርጓል። የመለስ ጀሌዎች በፈጠሩት ጦስ ብዙዎችም ወደ እስር ተግዘዋል። የዋልድባ መሬት ለሸንኮራ ልማት ተብሎ ለባእዳን ተሰጥቷል። ዛሬ ያልተነካ፤ ዛሬ ያላለቀሰ፤ ዛሬ ያላዘነ የለም።ሁሉም በአንድነት ተነክቷል። በአንድነት አዝኗል።

እንግዲህ መፍትሄው ምንድ ነው ?

መፍትሄው በዚያች አገር የግለሰቦችን መብት የሚያከበር የህግ የበላይነት መፍጠር ብቻ ነው። ይህ ደግሞ መለስ ዜናዊ በወንበሩ ላይ እያለ የሚታለም አይደለም። ስለዚህ መለስ ዜናዊ ስልጣኑን እንዲለቅ መጠየቅ የመፍትሄው ዋነኛው አካል ነው። መለስ ዜናዊ በጋምቤላ እና በኦጋዴን ለፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘር ማጥፋት ወንጀል ተመልካች ድርጅት አማካኝነት እጁ ተይዞ ለፍርድ እንዲቀርብ የሚፈለግ ግለሰብ ነው። እንዲህ ያለ ነፍሰ ገዳይ ግለሰብ አገራችንን ለመምራት የሞራልም ሆነ የአቅም ብቃት የለውምና ከተፈናጠጠበት ወንበር እንዲነሳ በአንድነት መጠየቅ የአገሪቷ ችግር መፍቻ ቁልፍ ነው።

መጂሊሱ በመውረዱ ሁለንተናዊ መፍትሄ አይመጣም። እውነተኛ መፍትሄ የሚገኘው በመስኪዶቻችን ውስጥ የንጹሃንን ደም ያፈሰሱ ግለሰቦች እጃቸው ተይዞ ለፍርድ ሲቀርቡ ነው። የአምልኮ መብታችን ይከበር ያሉ ዜጎችን አልቃይዳንና አልሸባብን ከመሰሉ ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች ጋር አስተሳስሮ የተናገረው መለስ ዜናዊ አለኝ ያለውን መረጃ ወይም በእርሱ አባባል "ማስረጃ" እያለ የሚመጻደቅበትን ለህዝብ ይፋ ያደረገ ግዜ ነው አሸባሪው ከጤነኛው የሚለየው።

የገዳማቱን መሬት በቃ መልሰናል ማለትም መፍትሄ አይሆንም።መፍትሄ የሚሆነው ገዳማቱንና አጠቃላይ ኦሮቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትንን ያዋረዱት፤ ለራሳቸው ክብር ሃውልት ያቆሙት፤ ለሲኖዶሱን ውስኔ አንገዛም ያሉት፤ በቤተ-ክርስትያኒቷ ውስጥ ዘረኝነትን የተከሉትና ባእድ ነውሮችን ያስገቡት ከመንበራቸው መነሳት ነው። በቤተክርስትያኒቷ ላይ ላደርሱት ኪሳራም ተጠያቂ የሚሆኑበት መንገድ ሲፈጠር ነው የተቋጠረው የሚፈታው ያዘነው እፎይ የሚለው።

ዛሬ በጋምቤላ ሃዘኑ ወደ ቁጣ ተቀይሯል። ጋምቤላዎች የአባቶቻችንን ምድር ለባእዳን አሳልፈን ሰጥተን ስደተኛ አንሆንም እያሉ ነው። ሙስሊሞች የምናመልከውን ለእኛ ተውልን ቢሉም መለስ ዜናዊ የሚሰማ ጆሮ ስለሌው አይሰማም ብሏል። ኦሮቶዶክሳዊያን ገዳማቶቻችንን ተውልን ቢሉም ሰሚ እያገኙ አይደለም። ይህ ሁሉ ጩኸት ወደ ቁጣ የሚቀየርበት ግዜ እየመጣ ነው።ህዝብ እንዲህ ያለ ውጥንቅጥ ውስጥ እየገባ ያለው አገሪቷ የምትገዛው በህግ ሳይሆን በመለስ ዜናዊ ስሜት ስለሆነ ብቻ ነው። የመለስ ዜናዊ ስሜት ደግሞ በጫት፤ በሲጋራ እና በልዩ ልዩ ናርኮቲክ ከኒኖች የተመረዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥላቻና ውሸት ስጋ ለብሰው የሚገለጡበት ነው።የዚህ ግልሰብ ስሜት ህግ የሆነበት አገር ውስጥ ህግ ዜጎችን ለማጥቂያ ይውላል እንጂ ለፍትህ ማስከበሪያ አይሆንም። የዚህ ግለሰብ ስሜት ህግ በሆነበት አገር ውስጥ ግጭትና መለያየት ይበዛል እንጂ ሰላምና አንድነት አይኖርም። የዚህ ግለስብ ስሜት ህግ የሆነበት አገር የአምልኮ ቦታዎች ይዋረዳሉ እንጂ አይከበሩም። ዜጎች ይከፋፈላሉ እንጂ ህብረት አይኖራቸውም።ዛሬ በኢትዮጵያችን እየታየ ያለው እውነት ይሄው ነው።

ስለዚህ መፍትሄው አንድና አንድ ነው።መለስ ዜናዊ ከተቆናጠጠበት ወንበር እንዲለቅና በህዝቡ የተመረጠ ወንድሞቼ፤ እህቶቼ፤ አባቶቼ፤ እናቶቼ፤ ልጆቼ፤ ወገኖቼ የሚል መሪ ስልጣኑን እንዲይዝ ማድረግ እና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ ነው።

መለስ ዜናዊ ከህግ በላይ ሁኖ፤ ህግን ዜጎችን ለማጥቂያነት እየተጠቀመ ባለበት በዚህ ግዜ ለተደቀኑብን ችግሮች መፍትሄ አይገኝም። መለስ ከስልጣኑ የወረድ እለት ግን ሰላም ይነግሳል፤ አንድነት ይመጣል፤ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል የእምነት ነጻነቶቻችን ሁሉ ይከበራሉ።ይህ በአገራችን እውነት እንዲሆን ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አሉ የሚባሉ መንገዶችን ሁሉ ይሄድባቸዋል ከሁሉም ጋር ተባብሮ ይታገላል። በዚህ ክፉ ግዜም የሙስሊሙም የክርስትያኑም ቀንደኛ ጠላት መለስ ዜናዊ እና ጉጅሌዎች ናቸውና ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች በአንድነት ቆመው ለነጻነታቸው መከበር መታገል አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

አሁን ያልተቆጣ ዜጋ መቼ ሊቆጣ ነው? አሁን እምቢ ለእምነቴ ያላለ መቼ እምቢ ሊል ነው? አሁን ዘረኝነት በቃ፤ ከፋፋይነት በቃ ዝሪፊያ በቃ ያላለ መቼ በቃ ሊል ነው? አሁን በአንድነት ያልቆመ መቼ በአንድነት ሊቆም ነው? በመካከላችን ጠብን ለመትከል የሚሠሩትን ብድኖች በቃ ለማለት ግዜሁ አሁን ነው።

በመጨረሻም ለዘመኑ ባለስልጣናት እንዲህ እንላለን "እግዚአብሄር የሚጠየፋቸው ስድስት ነገሮች አሉ። ሰባተኛውን ግን ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች፤ ትዕቢተኛ ዓይን፤ ሃሰተኛ ምላስ፤ ንጹህን ደም የምታፈስ እጅ፤ክፉ አሳብን የሚያበቅል ልብ፤ ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር፤ በሃሰት የሚናገር ሃሰተኛ ምስክር፤ በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ" በእግዚአብሄር የማያምን ባለሂሊና ሳይቀር እነዚህን ጥፋቶች አጥብቆ ይጠላቸዋል። ዛሬ በወንድማማቾች መካከል ጠብን ለመትከል የምትተጉ መለስ ዜናዊና ጉጅሌዎች ወዮላችሁ። በምድር ህግም ሆነ በሰማይ የሚያስጠይቃችሁን ወንጀል እየፈጸማችሁ መሆናችሁን አስታውሰናችሁ እናበቃለን።

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የህዝብ ድምጽ በመስረቅ አገራችንን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከግንቦት 7 ቀን ከ1997 ዓም ወዲህ በነበሩት ሰባት ዓመታት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወደ ፍጹማዊ አምባነንነት በመሸጋገር የመንግሥትን ሥልጣን በቤተሰብ የያዘበት፤ የሃብት ዘረፋ ተሰምቶ እማይታወቅበት ደረጃ የደረሰበት፤ የመለስ ዜናዊ ዘመዶችና አጫፋሪዎቹ በሃብት ላይ ሃብት፤ በምቾት ላይ ምቾች ሲደራርቡ ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን የእለት ጉርሱን እንኳን ማግኘት ወደማይችልበት የድህነት ደረጃ ቁልቁል የወረደበት ከመሆኑ አልፎ ኢትዮጵያዊያን የልባቸውን መናገር ቀርቶ ማሰብ እንኳን እንዳይችሉ ሂትለር ያልተጠቀመበት አይነት የፀረ-ሽብር ህግ የሚባል አፋኝ ህግ ወጥቶ የዜጎችን አንደበትና ህሊና ለመዝጋት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው ንቅናቄው በመግለጫው እንዳሰፈረው።

መግለጫው በመቀጠልም ይህ ሁሉ አፈናና ጭቆና ሳያንስ ህዝባችንን በድህነት አዳክሞ "ወይን ለኑሮ" በሚባል አዋራጅ ስልት ሰዎች ለመኖር ሲሉ የሥርዓቱ ተባባሪ እንዲሆኑለት ለት ተቀን እየዳከረ በመሆኑ ይህንን አዋራጅ ሁኔታ ለመቀየር ንቅናቄው ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በመመስረት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ነው።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊን በጂ 8 ስብሰባ ላይ መጋበዝ በመቃወም ኢትዮጵያዊያን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የኢትዮጵያ ህዝብ እየተፈናቀለና እየተገደለ ለነርሱ የሚሰጠው መሬት በኢትዮጵያና በህንድ መካከል ወደፊት ሊፈጥረው የሚችለው አደጋ መኖሩን አውቀው በመሬት ሺሚያው የተሳተፉ ኢንቨስተሮች በሰላም ወደአገራቸው እንዲመለሱ የጠየቁበትን የአቤቱታ ደብዳቤ ያስገቡት ሰላማዊ ሰልፈኞች የአገሪቱን ጥቅም አሳልፎ ከሚሰጠው መልስ ዜናዊ ጋር የሚፈጸም ማንኛውም አይነት ውል ወደፊት በሚመሰረተው የህዝብ መንግሥት ምንም አይነት ተቀባይነት እንደማይኖረው መግለጻቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና ያስረዳል።

መለስ ዜናዊ በካምፕ ዴቪድ ስብሰባ በሚሳተፍበት የፍታችን ቅዳሜ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ ስብሰባው ከሚደረግበት አዳራሽ ፊት ለፊት እንደሚደረግ ማርች ፎር ፍርዴም ከበተነው የጥሪ ደብዳቤ መረዳት ተችሎአል።

የግንቦት 7 ዝግጅት ክፍል በሰሜን አሜሪካ የሚገኝ አገር ወዳድ ሁሉ የፊታችን ሜይ 19 በሚደረገው በዚህ ተቃውሞ ሰልፍ ላይ ተገኝቶ የመለስ ዜናዊን ዘረኛነት እንዲያጋልጥ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል።

## በወያኔ እስር ቤቶች ውስጥ ከ400 በላይ የፖለቲካ እስረኞች ፍትህ አጥተው በመንገላታት ላይ መሆቸው ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን በ እጁ የገባውን መረጃ ጠቅሶ እንደዘገበው በመለስ ዜናዊ የአፈና መዋቅር ሰለባ የሆኑ በቃልቲና እና በቂልንጦ ማረሚያ ቤቶች ብቻ ብዛታቸው ከ400 በላይ የሆኑ የፖለቲካ እስረኞች መኖራቸው ታውቆአል። ኢሳት የሥም ዝርዝራቸውን ጭምር ማግኘቱን የገለጻቸው እነዚህ የፖለቲካ እስረኞች የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ባለመደገፋቸው የሃሰት ክስ ተፈብርኮባቸው ያለአግባብ ለአመታት ወሂኒ በመማቀቅ ላይ የሚገኙ ናቸው ። ከነዚህ ታሳሪዎች አብዛኞዎቹ ከግንቦት7 እና ከኦነግ ጋር በተያያዘ የፈጠራ ወንጀል መታሰራቸውን የሚገልጸው መረጃ በብሄር ተዋጽኦቸውም አብዛኞቹ አስረኞች የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች መሆናቸውን አስታውቆአል።

ከነዚህ ታሳሪዎች በአቶ አንዱአለም መዝገብ የተከሰሱ 24፣ በአቶ በቀለ ገርባ 9፣ በጄ/ል ተፈራ ማሞ 46፣ በአቶ ተሻለ በኬ ፣ 69፣ በአቶ አል አህመድ ሰኢድ 33፣ በአቶ አሸናፊ አዱኛ 22፣ በአቶ ጌትነት ገመቹ 20፣ በአቶ ደጃሳ ወርቁ፣ 22 እና በአቶ ደበላ ጣፋ 35 መሆናቸው ለአብነት ያክል ተጠቅሰዋል።

ከእነዚህ መካከል 217 እስረኞች ከእድሜልክ እስከ 15 አመታት የተፈረደባቸው ሲሆን፣ 184ቱ ደግሞ እስካሁን ፍርድ አላገኙም። አብዛኞቹ እስረኞች የመገናኛ ብዙሀንንና አለማቀፉ ማህበረሰብ የማያውቃቸው ናቸው ተብሎአል።

አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለስልጣኑ የሚያሰጋውን ሁሉ ለእስር በመዳረጉ ዘወትር በአለማቀፍ የሰብ አዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ይወቀሳል።

በተያያዜ ዜና በሰኔ ወር ውስጥ የአውሮፓ ህብረት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚፈጸመው ሰብአዊ መብት ጥሰት ለመነጋገር አንድ ጉባኤ ለማዘጋጀት እንዳቀደ ለማወቅ ተችሎአል። ኢሳት ታማኝ የዲፐሎማቲክ ምንጮችን ጠቅሶ እንደገለጸው ህብረቱ በአለም ደረጃ ታዋቂ ከሆኑት እና ብዙ የማግባቢያ (ሎቢ) ስራ ከሚሰራላቸው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ከመሳሰሉት እስረኞች በስተቀር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ እስረኞች መረጃ የለውም። በሰኔው ጉባኤ የእስረኞችን ስም ዝርዝርና ፎቶ በጉባኤ አዳራሹ ውስጥ ለማስቀመጥ እንቅስቃሴ መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል።

## መለስ ዜናዊ በአገራችን ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ወንጀል እንዲያቆም . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሆኖም አያውቅም፤ ወያኔ በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ሽብርተኝነት ያቁም፤ የአውሮፓ ህብረት ለመለስ ዜናዊ ሽብርተኛ አገዛዝ የሚያደርገውን እርዳታ አሁኑኑ ያቁም፤ ፍትህና ድሞክራሲን እንሻለን፤ እስርና ግዲያ ይቁም፤ ሁሉም ፖለቲካ እስረኞች አሁኑኑ ይፈቱ፤ ወዘተ የሚሉ ናቸው።

የሰላማዊ ሰልፉ አዘጋጆች በአገራችን ውስጥ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ እየተፈጸመ ነው የሚሉትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ዝርዝር፤ ዜጎችን በማፈናቀል ለውጪ ባለሃብቶች እየተቸበቸበ ስላለው መሬት፤ መንግሥት በሙስሊም እምነት ውስጥ ጣልቃ በመግባት ምዕመኑን እርስ በርስ ለማጋጨት እየፈጸማቸው ስላለው ወንጀሎች፤ ታሪካዊ ገዳማትን በልማት ስም ለማፍረስ እየተፈጸመ ስላለው ደባ፣ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ጋዜጠኞች ላይ እየተወሰደ ስላለው እስርና ግዲያ የሚያትት አቤቱታ ለኮሚሺኑ ጽ/ቤት ማስገባታቸውን ታውቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባሳለፍነው ቅዳሜ በሆላንድ በአምስተርዳም ከተማ ወያኔ ጥቂት ደጋፊዎቹን በድብቅ ሰብሰቦ ለአባይ ግድብ ድጋፍ እንዲያዋጡ ጠይቆ እንደነበረና ከተለያዩ የሆላንድ ከተሞች ብዙ ሰዎች ይመጣሉ ተብሎ ቢጠበቅም ከአስራ አንድ ያልበለጡ ቀንደኛ ደጋፊዎች ብቻ መገኘታቸውን ኢሳት በትናንትናው ዜገባው ገልጾአል።

እንደኢሳት ዘገባ የተፈለገው ያህል ሰው ባለተገኘበት የወያኔ ስብሰባ ለአባይ ቦንድ ግዢ ህብረተሰቡን የሚያስተባብሩ ሁለት ሁለት ተወካዮች በየከተማው ህዋስ በመጣል ቀጣይነትያለው ስራ ለመስራት በመስማማት፣ የቅስቀሳ ሲዲዎችን በማደል ስበሰባው ተጠናቋል። ወያኔ በሆላንድ በጠራቸው ተደጋጋሚ ስብሰባዎች ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ ስለገጠመው ህቡዕ በመግባት ስብሰባዎቹን በድብቅ ለመጥራት መገደዱ ብዙዎችን ያስገረመ ክስተት ሆኗል።

በተመሳሳይ መንገድም ወያኔ በሉክሰምበርግ ባለፈው ሚያዚያ ወር ሊያካሄድ የነበረው ስበሰባ ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ በማሰማታቸው መሰረዙ ታውቋል። በሉክዘምበርግ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንደገለጡት ኤፕሪል 29 ቀን በአባይ ግድብ ዙሪያ ሊካሄድ የነበረው ስብሰባ ኢትዮጵያውያን በመቃወማቸው ለሜይ 29 በድብቅ እንዲተላለፍ ተደርጓል። በብራሰልስ የሚገኘው የወያኔ ኢምባሲ ቅጥረኞች ስብሰባውን የሚቃወሙትን ኢትዮጵያውያንን ስልክ በመደወል ለማግባባት እና ለማስፈራራት ሙከራ ሲያደርግ መሰንበቱን የሚናገሩ ምንጮች ለሜይ 29 ሌላ ስብሰባ ሙከራ ለማድረግ ጥሪ ማስተላለፉን መተላለፉን አረጋግጠዋል።

በቤልጂዬም የሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ የሚቃወሙትን ኢትዮጵያዊያን ወደ አገራቸው ለጉብኙት እንዳይሄዱ የመግቢያ ቪዛ በመከልከል ለመበቀል እየጣረ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት (መጅሊስ) ፕሬዝዳንት መለስ ዜናዊ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በርሳቸውና ሃሳባቸውን በማይደግፉ አባቶች መካከል የተፈጠረው ክርክር እየተካረረ ሁዶ ውዝግብ መነሳቱንና ፓትርያርኩ፡-*መንግሥት አካል ጣልቃ ገብቶ ያነጋግረን" እስከማለት ደርሰው እንደነበረ ደጀሰላም ዘግቦአል።*

በውዝግብና አለመግባባት የተጀመረው የሲኖዶሱ ስብሰባ በትናትናው ዕለትም ቀጥሎ እንደነበር ታውቅቆአል። በዚህ አይነት እየተካሄደ ያለው የስንዶሱ ስብሰባ በምን እንደሚቋጭ ለማወቅ አንዳንድ የ እምነቱ ተከታዮች በጉጉት እየጠበቁ ቢሆንም ምንም የረባና ፋይዳ ያለው ነገር ላይ ሊደስር እንደማይችል ጉዳዩን የሚከታተሉ ሰዎች በ እርግጠኝነት ይናገራሉ።

በአባ ጳውሎስ የሚመራው የአገር ቤቱ ሲኖዶስ በዋልድባና በተቀሩት ገዳሞች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ጥፋት እንኳ ለማውገዝ ጉልበት አጥተው ሲልፈሰፈሱ በውጪ የሚገኘው ሲኖዶስ የወያኔን ጥፋት እርምጃ ለማስቆምና በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃገብነት ለማስቀረት ኢዮጵያዊያን በዘር በሃይማኖትና በጾታ ሳይከፋፈሉ አንድ ላይ ቆመው እንዲታገሉ ጥሪ ማስተላለፉ ይታወቃል።

## ግንቦት 7ን ለ7ኛ ጊዜ ስንዘክር ... (ከገፅ 1 የዞረ)

ግንቦት 7 በአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ያከናወናቸው ተግባራት በቂ ባይሆኑም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። ግንቦት 7 በአራት ዓመታት እድሜው ካከናወናቸው ተግባራት የሚከተሉትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

1. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ "ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ፀጥ አስደርጌዓለሁ" ባለበት ሰዓት "እንቢ! ለዘረኛ" ያሉ ወገኖች የተሰባሰቡበት በአገር ቤትና በውጭ አገራት ሰፊ መሠረት ያለው ድርጅት ለመሆን ችሏል።
2. የመለስ ዜናዊን የሚዲያ አፈናን በመገዳደር ኢትዮጵያዊያን ነፃ እና ሃቀኛ መረጃ የሚያገኙበትን መንገዶች በማፈላለግ ረገድ ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ ወደፊትም ያደርጋል።
3. በኢትዮጵያዊያን መካከል አድማሱን ያሰፋ ኅብረት እንዲኖር ጥረት አድርጓል። በዚህ ረገድ ተስፋ ሰጭ ሁኔታዎች እየታዩ ነው።
4. ግንቦት 7 ብዙዎች ለዓላማው መሳካት ሕይወታቸውን ሊሰውለት የሚፈቅዱለት፤ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ እረፍት የነሳ፤ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን ተስፋ የፈነጠቀ ድርጅት ለመሆን በቅቷል።
5. በራሱ በመለስ ዜናዊ ወታደራዊ፣ አስተዳደራዊ እና የስለላ መዋቅር ውስጥ በመግባት የመለስ አገዛዝ እንዳይረጋጋ ለማድረግ ችሏል።
6. የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ዘረኛ ባህርይ በኢትዮጵያዊያንና በውጭ አገራት ዜጎች ዘንድ እንዲታወቅ አድርጓል። በዚህም ምክንያት መለስ ዜናዊ ተራ አምባገነን ሳይሆን ዘረኛ አምባገነን መሆኑን በሰፊው እንዲታወቅ አድርጓል።

የመለስ አገዛዝን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን በጥንቃቄ በማጥናት ትግሉ የሚጠይቀውን ሁለገብ የትግል ስልት ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ያለ ድርጅት ሆኗል።

ይሁን እንጂ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አልተወገደም፤ ዲሞክራሲ በአገራችን አልሰፈነም። ይልቁንም አፈና፣ ስደት እና ድህነት በዝቷል። ምሬት በዝቷል። ድሆች አርሶ አደሮች እየተፈናቀሉ ነው። ገዳማትና መስኪዶች ተደፍረዋል። ኢትዮጵያዊያን በገዛ አገራችን ለባርነት ተዳርገናል። እናም ትግላችን ይቀጥላል።

በአሁኑ ሰዓት ሁኔታዎች እየተቀየሩ ነው። ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የወያኔን ጣልቃ ገብነት የተቃወሙበት ጽናት፤ ክርስቲያኖች የዋልድባ ገዳምን ለማዳን ያሳዩት መረባረብ፤ ከጉራ ፈርዳ ወረዳና አካባቢው ለተፈናቀሉ የአማራ አርሶ አደሮች መብት የታየው መቆርቆር፤ የመምህራን አመጽ፤ በጋምቤላ፣ አፋርና ኦጋዴን ያሉ ሁኔታዎችን ስንገመግም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባርነት አንገፍግፎት የሚነሳበት ቀን ደርሷል ብለን እናምናለን።

ከባርነት ነፃ ለመውጣት በጽናት መታገል ግድ ነው። እስካሁን ድረስም በመለስ ዜናዊ በሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጅሌ ላይ በጋራ ተነስተን ቢሆን ኖሮ ይኸን ያህል ጊዜ ሊፈነጭብን ባልቻለም ነበር። ዛሬም ተባብረን ተነስተን ራሳችን ካላደረግነው በስተቀር ይኸንን ጠላት ከጀርባችን የሚያወርድልን ሌላ አካል የለም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በግንቦት 7 ቀን 1997 አግኝተነው በማግሥቱ በጉልበት የተነጠቅነውን ነፃነት ለማስመለስ ለራሱ የገባዉን ቃል ዛሬም ህያው ነው። ግንቦት 7፣ የትግራይ ገዢ ጉድሌን ዘረኛ፣ አምባገነን ሥርዓትን ሁኔታዎች በፈቀዱለት መንገዶች ሁሉ ይዋጋል።

ፍትህ፣ ነፃነት እና ዲሞክራሲ ናፋቂው የኢትዮጵያ ሕዝብም በግንቦት 7 ጎን ቆሞ ትግሉን እንዲያፋፍም ወገናዊ የትግል ጥሪ ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org